የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ
AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

አስራ አንደኛ ዓመት ቁጥር 56 ሠመራ ጥር 2003 ዓ.ም.	በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነትየወጣ	11th year No. 56 samara ----- /2010

ማውጫ

የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ስራዎች ልማት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ..... ገጽ 1

አዋጅ ቁጥር 32/1998 ዓ.ም

የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ስራዎች ልማት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ

መግቢያ፣

ጥቃቅንና አነስተኛ ንግድን ማስፋፋት የክልሉን ህብረተሰቡ በተለይም በአነስተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኘውን የህብረተሰብ ክፍል የኑሮ ደረጃ በመቀየርና የገቢ ምንጩን በማሳደግ በክልሉ ብሎም በሀገር ግንባታ ሂደት ንቁ ተሳትፎ የሚያደርግበትን ሁኔታ ማመቻቸት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ም/ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 47(3)(ሀ) መሠረት ይህን አዋጅ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ #የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ስራዎች ልማት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 56/2 ዐዐ 3 ዓ.ም$ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር

1. # ቢሮ$ ወይም #ቢሮ ኃላፊ$ ማለት እንደቅደም ተከተሉ የንግድ'ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት ቢሮ ወይም ቢሮ ኃላፊው ነው።

2. # የጥቃቅን ንግድ$ ወይም #አነስተኛ ንግድ ስራ$ ማለት የኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት መስፈርቱ የሚወሰንላቸው የንግድ ስራዎች ማለት ሲሆን'የቴክኖሎጂና የምክር አገልግሎት ተቋማትን አይጨምርም ነው።

ክፍል ሁለት

ስለ ኤጀንሲው መቋቋም፣ ተጠሪነት፣ አላማ፣አደረጃጀትና ስልጣንና ተግባር

3. መቋቋም

1. የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ስራዎች ልማት ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ #ኤጀንሲ; ተብሎ የሚጠራና ህጋዊ ሠውነት ያለው ራሱን የቻለ የክልሉ መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. የኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለክልሉ ንግድ'ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት ቢሮ ይሆናል።

4. ዋና መስሪያ ቤት

የኤጀንሲው ዋና መስሪያ ቤት በሰመራ ከተማ ይሆናል።

5. አላማ

የኤጀንሲው ዓላማ በክልሉ የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ስራዎች እንዲያድጉና እንዲስፋፉ ድጋፍ የሚሰጡ ተቋማትን ማበረታታት'ማስተባበርና መደገፍ ይሆናል።

6. የኤጀንሲው ስልጣንና ተግባር

1. ኤጀንሲው በህግ የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስፈልገውን ሥልጣን ሁሉ ይኖረዋል።

2 u ክልሉ ¨<eØ Ønp”“ ›’e}— ›=”}`ý^Ã´ እ”Ç=eóñ ÁÅ`ÒM&

3 u ክልሉ ¨<eØ ŸS”ÓY ቃ©“ S”Óe ቃ© "MJ’< É`Ï„‹ Ò` Ó”–<’ƒ uSõÖ` ¾Ønp”“ ¾›’e}— Y^ T%u^ƒ ÉÒõ እ”Ç=ÁÑ–< G<’@ቃ‹” ÁS‰‰M& u}KÃU ¾TU[‰“ ¾SgÝ x ቃ‹' ¾óÃ“”e“ ¾wÉ` ›ÑMÓKA„‹' ¾Ø_ °n“ ¾TU[‰ Sd]Á‹ እ”Ç=G<U ¾SW[ƒ MTƒ ›¨<ቃ a‹ ¾T>ÁÑ–<uƒ” G<’@ቃ ÁS‰‰M&

4 ¾Ønp”“ ›’e}— ንግድ ተቋም TcMÖ— T°ŸLƒ እ”Ç=ssS< G<’@ቃ‹” ÁS‰‰M&u ክልሉ ¨<eØ uØnp”“ u›’e}— ›=”}`ý^Ã´ K}WT\ ¾lw[}cw ¡õKA‹ YMÖ“‹“ ›¨<Å-`°Ä‹ እ”Ç=²ÒÌ ÁÅ`ÒM' Áe}vw^M&

5 u ክልሉ ¨<eØ ¾T>Ñ–<ƒ” Y^ ›Ø ¾J’< ¨×„‹“ c?„‹ ›U^‹ ²?Ò K=ÁÅ`Ñ< ¾T>‹K< ¾Ønp”“ ›’e}— Y^ –aË¡„‹ ÁÖ“M'እ”Ç=Ö’< ÁÅ`ÒM'¾T>SKŸ}¨< ›"M c=ðpÉU }Óv^© ÁÅ`ÒM'¨<Ö?ƒ TeÑ–ቃ†¨<” ÃŸቃ}LM&

6 ¾Ò^ TU[‰ T°ŸLƒ □እ¾}Ñ’u< K›”kdnj‹ እ”Ç=cÖ< ÁÅ`ÒM:: ¾T°ŸL~” ›ÖnkU“ ›e}ÇÅ` SS]Á Á¨×M' ›c^\ uSS]Á¨< Sc[ƒ SJ’<” ÃŸቃ}LM&

7 ¾U`ƒ SgÝ“ TdÁ T°ŸL~” ›ÖnkU“ ›e}ÇÅ` SS]Á Á¨×M'›c^\” uSS]Á¨< SW[ƒ SJ’<” ÃŸቃ}LM&

8 ›”kdnj‹ U`„‰†¨<”“ ›ÑMÓKA቎†¨<” K}ÖnT>¨< KTe}ª¨p እ”Ç=‹K<“ ¾ÑuÁ °ÉL†¨<” KTeóf ›?Ó´u=i”“ v³a‹ እ”Ç=²ÒÌ ÁÅ`ÒM&

9 u}KÁ¿ ¾Y^ ²`ö‹ ¾}cT\ }sTƒ እ”Ç=KS<“ Y^†¨< k×Ã’ƒ እ”Ç=•[¨< ¾”ÓÉ MTƒ ›ÑMÓKAƒ ¾T>cØuƒ” S”ÑÉ ÁS‰‰M&

10 ¾›”kdnj‹ U`ƒ“ U`቎T’ƒ” KTdÅÓ ¾}hhK<“ ²S“© Sd]Á‹ ¾T>c\uƒ“ Y^ LÃ ¾T>¨<K<uƒ” S”ÑÉ ÁS‰‰M&¾›”kdnj‹ ›pU” KSÑ”vƒ ¾S<Á“ ¾Y^ ›S^` eMÖ“‹ እ”Ç=cÖ< ÁÅ`ÒM&

11 ›”kdnj‹ uÓM' u”ÓÉ' u%w[ƒ Y^ TIu` ¾}Å^Ì“ IÒ© ¾J’< ¾T>c\uƒ” S”ÑÉ ÁS‰ ‰M::

12 ¾S[Í“ ¾U¡` ›ÑMÓKAƒ K}ÖnT>‹ ¾T>cØuƒ” Y`¯ƒ Ã²[ÒM::

7. አቋም

1. ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉትን አካላት ይኖሩታል

ሀ/ የስራ አመራር ቦርድ (ከዚህ በኋላ#ቦርዱ$ እየተባለ የሚጠራ)

ለ/ ዋና ስራ አስኪያጅ እና

ሐ/ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ሠራተኞች

2. የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስኪያጅ በክልሉ ርዕስ መስተዳድር ይሾማል ።

3. የዋና ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነት ለክልሉ ንግድ'ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ ይሆናል።

8. ስለ ቦርዱ አባላት

1. የመንግስት መስሪያ ቤቶችና ከግሉ ዘርፍ የተውጣጡ በመንግስት የሚሰየሙ አስራ አንድ አባላት ይኖሩታል።

2. የቦርዱ ሰብሳቢ ከአባላቱ መካከል በመንግስት ይመደባል።

9. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል

1. የኤጀንሲውን ስራዎች በሚመለከቱ የፖሊሲና ስትራቴጂ ጉዳዮች ላይ እየመከረ ለቢሮ ኃላፊው የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል።

2. የኤጀንሲውን የረጅምና አጭር ጊዜ ዕቅዶች 'ዓመታዊ የስራ ፕሮግራምና በጀት መርምሮ ለቢሮ ኃላፊው ማቅረብ'ሲፈቀድም አፈጻጸሙን መቆጣጠር ።

3. የሲቪል ሰርቪስ ህግን መሰረታዊ መርሆዎች በመከተል የኤጀንሲው ሰራተኞች የሚቀጠሩበትንና የሚተዳደሩበትን ረቂቅ መመሪያ በማዘጋጀት ለቢሮው ኃላፊው ማቅረብና ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ ።

4. ለዋናው ስራ አስኪያጅ አጠቃላይ የስራ መመሪያ መስጠት።

5. ለዋና ስራ አስኪያጁ በቀጥታ ተጠሪ የሆኑ የኤጀንሲው የስራ ኃላፊዎች ቅጥር'ምደባና ስንብት ማጽደቅ::

10. የቦርዱ ስብሰባ

1. ቦርዱ በየሶስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል። ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።

2. በስበሰባው ላይ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።

3. ቦርዱ ውሳኔ የሚያስተላልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል። ሆኖም የተሰጠው ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ወሳኝ ድምጽ ይሆናል።

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1፣2 እና 3 እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስነ-ስርአት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

11. <u>የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስኪያጅ ስልጣንና ተግባር፣</u>

ዋና ሥራ አስኪያጅ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሰረት የኤጀንሲውን ስራዎች ይመራል'ያስተዳድራል::

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው አጠቃላይ ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋናው ስራ አስኪያጅ

ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ /6/ ሥር ለኤጀንሲው የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል::

ለ. ¾›?Ë”c=¨<” ሰራተኞች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው ሁኔታ በሚጸድቀው መመሪያ መሰረት ይቀጥራል'ያስተዳድራል'ያሰናብታል'

2. የኤጀንሲውን የስራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል'ሲፈቀድም ስራ ላይ ያውላል::

3. ¾›?Ë”c=¨<” ÖpLL ¾›c^` አፈጻጸምና ሂሳብ ሪፖርት ለቦርዱ ያቀርባል::

4. Ÿfe}— ¨Ñ•‹ Ò` uT>ÁÅ`Ò†¨< Ó”–<’„‹ ›?Ë”c=¨<” Ã¨¡LM::

5. K›?Ë”c=¨< e^ pMØõ“ uT>ÁeðMÓ SÖ” eM×”“ }Óv\” uŸòM K ኤጀንሲው ኃ Lò‹ እ“ c^}™‹ u¨<¡M“ K=Áe}LMõ Ã‹LM::

6. ሌሎች አግባብነት ያላቸውና ተጨማሪ ሥራዎችን ያከናውናል።

<u>ክፍል ሶስት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

12. በጀት

የኤጀንሲው በጀት ምንጮች ከሚከተሉት ይሆናል።

1. የክልሉ መንግስት በሚሰጥ የበጀት ድጎማ'
2. ከሚሰበሰበው የአገልግሎት ክፍያ' እና
3. ከማንኛውም ሌላ ምንጭ

13. የሂሳብና መዛግብት አያያዝ

1. ኤጀንሲው የተሟላና አግባብነት ያላቸው የሂሳብ መዛግብትን ይይዛል
2. የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብትና ሌሎች ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየአመቱ በክልሉ ዋና ኦዲተር መ/ቤት ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር ይመረመራል።

14. ደንብ የማውጣት ስልጣን

በዚህ አዋጅ መሰረት የክ MK< Se}ዳድር U ክ` u?ት ይህን አዋጅ KTe ፈጸ U የ T>ያ e ች M ደንብ K=ያወጣ ይች LM::

15. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሠመራ ---------- 2ዐዐ3 ዓ.ም.

እስማኤል ዓሊ ሴሮ

የአፋር ብ/ክ/መንግስት

ርዕስ መስተዳድር